**የሰ/መ/ቁጥር -** 231064

መጋቢት 27 ቀን 2015 ዓ.ም

**ዳኞች:-**

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻዉ አዳነ

ተሾመ ሽፈራዉ

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካቾች:-** 1. ወ/ሮ ሻሺ ሙሉ
2. አቶ ባዩ ሙሉ
3. ወ/ሮ አየለች ሙሉ
4. አቶ ለማ ሙሉ
5. ወ/ሮ መስከረም ሙሉ
6. አቶ አቡ ሙሉ
7. ወ/ሮ ወርቅነሽ ሙሉ
8. አቶ ግርማ ሙሉ

(1–8) ጠበቃ አለሙ ደገፉ - ቀረቡ

**ተጠሪ:-** አቶ ሙሉ ቦጋለ - ጠበቃ በጂጋ ሶሬቻ - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

**ፍርድ**

ጉዳዩ የዉርስ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን፣ ክርክሩ በተጀመረበት በቢሾፍቱ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካቾች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነሐሴ 27 ቀን 1988 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩትን የእናታቸዉ የወ/ሮ አቦዘነች ቱፋ ንብረት ተጠሪ ይዞ የሚገኝ መሆኑን ጠቅሰዉ ድርሻቸዉን እንዲያካፍሏቸዉ የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ ተጠሪ በበኩላቸዉ ክሱ የቀረበዉ የአስር ዓመት ጊዜ ካለፈ በኋላ መሆኑን እንዲሁም በ1999 ዓ.ም አመልካቾች በዚሁ ጉዳይ ላይ ክስ አቅርበዉ ጉዳዩን ባለመከታተላቸዉ መዝገቡ የተዘጋ በመሆኑ በድጋሚ የቀረበ ነዉ በማለት የመጀመሪያ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የወረዳዉ ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካቾች እናታቸዉ ሲሞቱ ዕድሜያቸዉ ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ስለመሆኑ እንዲሁም ቤትና ይዞታዉን ከተጠሪ ጋር ሲጠቀሙ የነበሩ ስለመሆኑ በማስረጃ አላረጋገጡም፤ በመሆኑም የአስር ዓመት ጊዜ ካለፈ በኋላ የእናታቸዉን ድርሻ የሚኙ እናታቸዉ ባል ከነበሩት ተጠሪ ለመካፈል ያቀረቡት ዳኝነት በይርጋ ይታገዳል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝ ተቀባይነት በማጣቱ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን፣

ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በበኩሉ መዝገቡን አስቀርቦ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ የዉርስ ንብረት ሰጥቻቸዋለሁ በማለት የተከራከሩ በመሆኑ በይርጋ አይታገድም፤ ተጠሪ ሰጥቻቸዋለሁ ብለዉ ነገር ግን መስጠታቸዉን ያላረጋገጡ በመሆኑ ተጣርቶ ዉሳኔ ሊሰጥበት ይገባል የሚል ይዘት ያለዉ ምክንያት በመስጠት የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ ሽሮ መዝገቡን ወደ ስር ወረዳዉ ፍርድ ቤት መልሶታል፡፡

ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን፣ ሰበር ሰሚዉ ችሎት በበኩሉ የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ ተጠሪ የዉርስ ድርሻ ስላላካፈለን ያካፍለን የሚል ሆኖ እያለ ከተጠየቀዉ ዳኝነት ዉጪ በመዉጣት ተጠሪ አካፍያለሁ ማለታቸዉን መሠረት በማድረግ ክሱ በይርጋ አይታገድም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ የክርክር አመራር ሥርዓትን የተከተለ ባለመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነዉ በማለት ሽሮ በስር በወረዳዉ ፍርድ ቤት እና በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚሁ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካቾች ሐምሌ 13 ቀን 2014 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በጠበቃቸዉ አማካይነት በቀረበ የሰበር አቤቱታ አከራካሪ የሆነዉን የዉርስ ቤትና ይዞታን ከተጠሪ ጋር በጋራ ስንጠቀምበት ቆይተን ተጠሪ በ2013 ዓ.ም እንዲያካፍለን በሽማግሌዎች ጠይቀን ከተወሰኑት ንብረቶች ዉጪ አላካፍልም በማለቱ ምክንያት ያቀረብነዉን ዳኝነት በጋራ ስንጠቀምበት እንደነበረ ሳይጣራ በይርጋ ይታገዳል ተብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን ጠቅሰዉ ታርሞ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የሰበር አቤቱታዉ ተመርምሮም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ዉሳኔ ባልሰጠበት እና ይርጋን ጨምሮ ተጣርቶ ዉሳኔ እንዲሰጥበት በመለሰበት ሁኔታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክሱ በይርጋ ይቋረጣል በማለት የመወሰኑን አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪ ጥቅምት 16 ቀን 2015 ዓ.ም አዘጋጅተዉ ባቀረቡት መልስ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በዝርዝር በመጥቀስ ጸንቶ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾች ጥቅምት 30 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል፣ ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታዉን ለማስቀረብ በአጣሪ ችሎት የተያዘዉን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ተጠሪ የእናታቸዉን የዉርስ ሀብት እንዲያካፍላቸዉ ዳኝነት በመጠየቅ ነዉ፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ባቀረቡት የመጀመሪያ መቃወሚያ መሠረት ክሳቸዉ በይርጋ የሚታገድ መሆን አለመሆኑን በመወሰን ረገድ ግምት ዉስጥ መግባት ያለበትም ይሄዉ የክሳቸዉ ምክንያት ነዉ፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የወረዳዉ ፍርድ ቤትም ይህንኑ መሠረት በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክር የሰማ ሲሆን፣ አመልካቾች የዉርስ ንብረቶቹን ከተጠሪ ጋር በጋራ ሲጠቀሙበት እንደነበረ እንዲሁም ከአመልካቾች የተወሰኑት ዕድሜያቸዉ ያልደረሰ መሆኑን ጠቅሰዉ ይርጋ ሊቋረጥ እንደሚገባ የተከራከሩ ቢሆንም ይህን ክርክራቸዉን በማስረጃ ማረጋገጥ ያልቻሉ መሆኑን ጠቅሶ ክሳቸዉ በአስር ዓመት ይርጋ ይታገዳል በሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱን የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ የፍሬ ነገር ድምዳሜ ተቀብሎ የወረዳዉን ዉሳኔ ያጸና ሲሆን፣ ከላይ እንደተገለጸዉ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክሱ በይርጋ አይታገድም በማለት ሲወስን መሠረት ያደረገዉ ተጠሪ ድርሻቸዉን ሰጥቻለሁ ብለዉ የተከራከሩ መሆኑን በመጥቀስ ሲሆን፣ ወደ ስር ፍርድ ቤት

የመለሰዉም የይርጋ ጉዳይ እንዲጣራ ሳይሆን ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን የዉርስ ንብረት አጣርቶ እንዲወስን ስለመሆኑ የዉሳኔዉ ይዘት ያስገነዝባል። ይሁንና፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ላይ እንደተመለከተዉ፣ ተጠሪ ለአመልካቾች ድርሻቸዉን ሰጥቻለሁ በሚል ያቀረቡት መከራከሪያ በክርክር ሂደት ተጣርቶ ዉሳኔ የሚሰጥበት ሲሆን ይህም የሚሆነዉ ከይርጋ ጋር በተያያዘ በተጠሪ የተነሳ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዉድቅ ከተደረገ በኋላ መሆኑ እሙን ነዉ።

በመሆኑም ተጠሪ ለአመልካቾች ድርሻቸዉን ሰጥቻለሁ የሚል ክርክር በፍሬ ነገር ደረጃ ማቅረባቸዉ ክሱ በይርጋ ቀሪ እንዳይሆን ምክንያት ሊሆን የማይችል በመሆኑ፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበትን ድምዳሜ በመሻር ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የወረዳዉን ፍርድ ቤት ዉሳኔ በማጽናት ዉሳኔ መስጠቱ በአግባቡ ነዉ ከሚባል በስተቀር ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10(1/ሐ እና መ) ላይ ከተመለከተዉ አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት የለም። ስለሆነም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል።

**ዉሳኔ**

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 394193 ላይ ሚያዝያ 25 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል።
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ።

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም